# የሆቴልና ቱሪዝም
# ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል

## CATERING AND TOURISM TRAINING CENTER

በማህበራዊ ገጾቻችን ይከታተሉን

www.ctti.edu.et

Catering & Tourism Training Institute

በህዝብና
ዓለም አቀፍ
ግንኙነት ዳይሬክቶሬት
የተዘጋጀ

ህዳር / 2013 ዓ.ም

ቅጽ 3 ቁጥር 1

# ዜና መጽሔት
# News Letter

# በውስጥ ገጾች


1. ወቅታዊ ጉዳዮች
2. ሰልጣኞችን ለመቀበል የተደረገ ዝግጅት
3. የተቋሙ የስራ እንቅስቃሴ



የማሰልጠኛ ማዕከሉ ሞዴል ሆቴል የሆነው ገነት ሆቴል ለሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ለገበታ ለሀገርና ለህዳሴ ገድብ 2.5 ሚሊዮን ብር ድጋፍ አደረገ፡፡
ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ህዳር 18/2013 ዓ.ም

የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ማዕከል ሞዴል ሆቴል የሆነው ገነት ሆቴል ለአገር መከላከያ ሰራዊትና ለሁለት አገራዊ ፕሮጀክቶች ማስፈጸ-ሚያ የ2 ነጥብ 5 ሚሊየን ብር ድጋፍ አደረገ፡፡

ተቋሙ በሕግን ማስከበር ዘመቻ ለተሰማራው የአገር መከላከያ ሰራዊት አንድ
ሚሊዮን ብር
ድጋፍ ያደረገ ሲሆን፤ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የአንድ ሚሊዮን ብር እንዲሁም ለ"ገበታ ለሀገር" ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ግማሽ ሚሊዮን ብር አበርክቷል፡፡



የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትሯ ዶክተር ሂሩት ካሳው "ድጋፉ ሰራዊቱ የሚያካሂደውን የሕግ ማስከበር ዘመቻ በመደገፍ አገራዊ የልማት ፕሮጀክቶችን ማስቀጠል እንደሚቻል ለማሳየት ነው" ብለዋል፡፡
ተቋማት ለአገር መከላከያ ሰራዊት ከሚያደርጉት ድጋፍ በተጓዳኝ አገራዊ የልማት ፕሮጀክቶችን ለማስቀጠል ድርሻቸውን እንዲወጡም መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ማዕከል ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ድጋፉ ሰራዊቱ እያደረገ ያለውን የሕግ ማስከበር ሥራ ለመደገፍና አገራዊ የልማት ፕሮጀክቶችን ለማስቀጠል ድጋፉ መደረጉን ተናግረዋል፡፡

የአገር መከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ማርታ ሉዊጂ ለተደረገው ድጋፍ ምስጋና አቅርበው፤ "የተደረገው ድጋፍ ለሰራዊቱ ትልቅ ሞራላዊና ቁሳዊ እገዛ ያደርጋል" ብለዋል፡፡



የታላቁ ኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አረጋዊ በርሄ በበኩላቸው ተቋሙ ለሰላም ማስከበርና ለአገራዊ ፕሮጀክቶች ላደረገው ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል፡፡
ኢትዮጵያውያን ሕግን ለማስከበር ለሚዋደቀው ሰራዊትና ለግድቡ የሚያደርጉትን ድጋፍ እንዲያጠናክሩም ጠይቀዋል፡፡
ለግድቡ ግንባታ የሚደረገው ሕዝባዊ ተሳትፎ መጠናከሩም በሥነ ሥርዓቱ ላይ ተገልጿል፡፡
በአገር አቀፍ ደረጃ በ"ገበታ ለሀገር" ለተያዙት የጎርጎራ፣ ኮይሻና ወንጪ ፕሮጀክቶች የሚደረገው ተሳትፎ እንዲጎ-ለብትም ጥሪ ቀርቧል፡፡




የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴርና ተጠሪው ተቋማት ጋር በመሆን "ደሜን ለሀገር መከላከያ ሰራዊት" በሚል የደም ልገሳ መርሀ ግብር አካሂዷል፡፡
ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ሕዳር 10/2013 ዓ.ም

በመርሃግብሩ የባህልና ቱሪዝም ሚንስትር ዶ/ር ሂሩት ካሰው ሀገር እንዲኖር ኢትዮጵያ እንደሀገር እንድትቀጥል የሰላም እና ጸጥታ ሰንደቅ የሆነው የሀገር መከላከያ ሰራዊት መኖር ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡
የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ሰራተኞችም በበኩላቸው በቀጣይ በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ከሀገር መከላከያ ሰራዊት ጎን ለመቆም ዝግጁ መሆናቸውን ተናግሯል፡፡



# ስልጣኞችን ለመቀበል የተደረገ ዝግጅት







የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ስልጠና ለመጀመር ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል፡፡
ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ህዳር /2013 ዓ.ም
በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት ተቋርጦ ነበረውን የኮድ19 ጥንቃቄ ፕሮቶኮልን በጠበቀ መልኩ ስልጠና ለመጀመር የአስተዳደራዊና አካዳሚክ ዝግጅት ተደርጓል፡፡

የኮሮና ቫይረስ ጥንቃቄ ፕሮቶኮልን ለመጠበቅ እንዲቻል በተቋሙ ውስጥ የተለያዩ ኮሚቴዎች ተቋቁመው አስፈላጊውን የእድሳት (maintenance) ስራዎች፣ የጽዳት ግብዓቶችን የማዘጋጀት፣ ክፍል ውስጥ ርቀትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችና ሌሎችም አስፈላጊ ግብዓቶችን የሚሟላት ስራ ተሰርቷል፡፡

በዚህም መሰረት ለምሳሌ ከዚህ በፊት እስከ ሰላሳ ሰው የሚይዙ የስልጠና ክፍሎች አሁን እስከ አስራ አምስት ሰልጣኞች ብቻ እንዲማሩበት ይደረጋል፡፡










የማሰልጠኛ ማዕከሉ በ2013 ዓ.ም የሚሰጠውን ስልጠና ወቅቱን ያገናዘበና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ለማስቀጠል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ተገለጸ፡፡
ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ መስከረም 11/2013 ዓ.ም

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል በ2013ዓ.ም የሚሰጠውን ስልጠና ወቅቱን ያገናዘበና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ለማስቀጠል እንዲቻል የመምህራን የተግባር አቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን በማዕከሉ የምግብና መጠጥ ክፍል ኃላፊ አቶ ስንታየሁ ወርቁ ገልጸዋል፡፡

ሰሞኑን በተለይ የሆቴልና ደጋፊ ትምህርት ዘርፍ አሰል-ጣኞች በዶሆ ሎጅ፣አዳማ ሀይሌ ሪዞርት፣አብጃታ ሻላፓርክ ውስጥ የሚገኙ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪድርጅቶችና ዳሽን ቢራ ፋብሪካ ላይ የመስክ ጉብኝት አድርጓል ፡፡
የአሰልጣኞች የመስክ ጉብኝቱ ተቋማቱ የሚሰጡትን አገል-ግሎት ፣ያላቸውን ፋሲሊቲ እና ከኮቪድ 19 ጋር ተያይዞ የሚያደርጉትን ጥንቃቄ በማየት የስልጠና ክፍተቶችን



ለመለየት፣ የተገኙ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለስልጠና ጥራት ለማዋልና የማማከር አገልግሎትን ለመስጠት ተቋ-ማዊ ትስስር ለመፍጠር እንደሚያስችል አቶ ስንታየሁ ወርቁ ገልጸዋል፡፡

የመስክ ጉብኝቱን የተሳተፉት የምግብ ዝግጅት አሰልጣኝ ሺመልስ ዘገየ ለሚሰጡት ስልጠና ግብዓት የሚሆኑ አዳዲስ ልምዶችና ተሞክሮዎችን አግኝተናል ብለዋል፡፡
ሆቴሎችና ሎጆች የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ መከላከያ መንገዶች ላይ ክፍተቶች የሚታዩ በመሆኑ በአግባቡ የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

# ለተቋሙ የተደረጉ ድጋፎች(ከኢምባሲዎች)






የፈረንሳይኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያግዝ መጽሐፍት
በስጦታ ተበረከተ
ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ሕዳር 10/2013 ዓ.ም
የፈረንሳይ ኤምባሲ ለፈረንሳይኛ ቋንቋ ትምህርት
የሚያግዝ መጽሐፍትና ሌሎች 21 ዓይነት አጋዥ
መሳሪያዎችን በስጦታ አበረከተ፡፡

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ከፈረንሳይ ኤምባሲ እና ከኢትዮ አሊያንስ ፍራንሴ ጋር በተደረገው ስምምነት መሰረት በዛሬው ዕለት ለፈረንሳይኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ የሚሆኑ መጽሐፍት፣ የኦዲዮና የቪዲዮ መርጃ መሳሪዎች ስጦታ ተበርክቶለታል፡፡

ስጦታውን የተረከቡት የተቋሙ ምክትልዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ስጦታውን በተረከቡበት ወቅት እንደ-ተናገሩት ተ ቋማችን የፈረንሳይኛ ቋንቋ ላለፉት 51 ዓመታት የስልጠናው አንዱ አካል አድርጎ ሲያስተምር የቆየ መሆኑን ገልጸው ሥጦታው ቋንቋውን በተሻለ ጥራት ለማስተማር እንደሚረዳ እና ሰልጠኞች ቋንቋውን ክፍል ውስጥ ከሚሰጣቸው ትምህርት ባሻገር በአጋዥ መጽሐፍቱ የበለጠ ዕውቀት እንደሚጨብጡ የሚያስች-ላቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ስጦታውን የፈረንሳይ ኤምባሲ ተወካይ ክሌር ፑንቱስ በቀጣይ ለቱሪዝም ትምህርት አጋዥ የሆኑ የፈረንሳይኛ ቋንቋ አጋዥ መሳሪያዎችን እያዘጋጁ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ጤንነትን ለመጠበቅና በሽታን ለመከላከል የሚሆኑ ባህላዊ
ምግቦችን ከዘመናዊ የትምህርት ስርዓት ጋር በማስተሳሰር
በሆቴሎችና ምግብ ቤቶች ጥቅም ላይ በሚውልበት ሁኔ-
ታዎች ላይ ውይይት ተደረገ፡፡
ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ህዳር 22/2013 ዓ.ም

የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ማዕከል የምግብ ዝግጅት መምህራን፣ የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተና ሀኪም አበበች ሺፈራው በተገኙበት ጤንነ-ትን ለመጠበቅና በሽታን ለመከላከል የሚሆኑ ባህላዊ ምግቦችን ከዘመናዊ የትምህርት ስርዓት ጋር በማስተሳሰር በሆቴሎችና ምግብ ቤቶች ጥቅም ላይ በሚውልበት ሁኔታዎች ላይ ውይይት አደረጉ፡፡

በሀገራችን በባህላዊ መልክ የሚዘጋጁ ምግቦች በርካታ መድሃኒትነት ያላቸው የምግብ አይነቶች በመኖራቸው ይህን ከትምህርት ስርዓት ጋር በማስተሳሰር ስልጠና በመስጠትና አገልግሎት ላይ ማዋል ለህበረተሰቡ ጤንነት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ሀኪም አበበች ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ውይይት በኋላ የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች፣ የባህላዊ ምግቦች ዝግጅት አውደ ርዕይና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች መዘጋጀት እንዳለባቸው ምክክር ተደርጓል፡፡





## በቱሪዝም ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የሰው ሃይል ለማፍራት እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ሕዳር 10/2013 ዓ.ም

የሆቴልና ቱሪዝም ማስልጠኛ ማዕከል የቱሪዝም ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን ብቃት ያለው የሰው ሃይል ለማፍራት እየሰራ መሆኑን የቱሪዝም ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ቡዜና አልከድር ገለጹ። የሆቴልና ቱሪዝም ማስልጠኛ ማዕከል የፌዴራልና የክልል የዘርፉ ሴክተሮች የቀጣይ አስር ዓመት መሪ አቅድ ላይ በአዳማ ከተማ ምክክር አድርጓል። ማዕከሉ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ የልህቀት ማዕከል እንዲሆን በተለይ በሰው ሃይል ልማት፣አቅም ግንባታ፣ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ዘርፉን በአግባቡ መደገፍ የሚያስችል አሰራር፣ የህግ ማእቀፎችና አደረጃጀትን ማሻሻል ላይ ትኩረት ማድረጉን ተናግረዋል። "በቂ የሰው ሃይል ልማት፣ አደረጃጀትና አሰራር መፍጠርና የዘርፉን ሽግግር ማፋጠን የቀጣይ አስር ዓመት የትኩረት አቅጣጫችን ነው" ብለዋል። በተለይ የሀገሪቱን የቱሪዝም ሴክተር ተወዳዳሪ ለማድረግ በመዳረሻዎች፣ በቱሪዝም ገበያ ማስፋፍያና የሰው ሃብት ልማት በእቅዱ ቀዳሚውን ትኩረት ያገኙ መሆናቸውን አመልክተዋል።




"ኢንዱስትሪው በስራ ዕድል ፈጠራ፣በኢኮኖሚ ልማትና እድገት ላይ ወሳኝ ሚና እንዲኖረው ብቃት ያለው የሰው ሃይል ማፍራት ይገባል" ያሉት ደግሞ የማዕከሉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ናቸው። "የትላልቅ ሆቴሎች ማናጀሮች፣ሱፐርቫይዘሮችና ሼፎች ከውጭ ይመጣሉ" ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ማዕከሉን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ማሰልጠኛ የልህቀት ማእከል በማድረግ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት መታ-ቀዱን አመላክተዋል።

"በሀገሪቱ በሆቴልና ቱሪዝም ማስልጠኛ ማእከላት ላይ የሚሰሩ ከ140 በላይ ተቋማት አሉ" ያሉት አቶ ገዛኸኝ የቱሪዝም ዘርፉን እድገት በእውቀት ለመምራትና ለመ-ደገፍ የሚያስችል የሰው ሃይል ማፍራት አሁንም ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ መሆኑን አስታውቀዋል።





## የማሰልጠኛ ማዕከሉ አሰልጣኞች የሙያና ማማከር አገልግ-ሎት የሥራ ላይ ስልጠና ሰጡ።

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ጥቅምት 24/2013

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል አሰልጣኞች የሙያና ማማከር አገልግሎት የሥራ ላይ ስልጠና ተሰጠ። በሃገራችን እንዲሁም በዓለም የኮሮና ቫይረስ ከተከሰተ በኋላ በሆቴሎችና በቱሪስት መዳረሻዎች ላይ ያደረሰው ተጽዕኖ ከባድ በመሆኑ የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሰፊ ጥናት ማጥናቱ ይታወቃል።



በጥናቱ የተነሱት ዋና ዋና ችግሮች የተባሉትን ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚመለከታቸውን በመተግበር ላይ ይገኛሉ። ማሰልጠኛ ማዕከሉ የራሱን ኃላፊነት ማለትም ሙያዊ ስልጠናና የማማከር አገልግሎት ላይ የታየውን ክፍተት ለመሙላት በሀገሪቱ ባሉት ሆቴሎችና ቱሪስት መዳረሻዎች በሁለት ዙር ለመስራት አቅዶ የመጀመሪያው ዙር 50 መምህራንን በማሳተፍ ከ20 በላይ ከተሞች ባሉ ሆቴሎችና ሪስቶራንቶች እንዲሁም የቱሪስት መዳረሻዎች ኮቪድ እያለ ስራቸውን በጥንቃቄ እንዴት መፈጸም እንዳለ-ባቸው የስራ ላይ ስልጠናና ማማከር አገልግሎት ተሰጠ። ስልጠናውንና የማማከር አገልግሎቱን ከሰጡት አሰልጣኞች መካከል አሰልጣኝ አዲስ ዓለም ልውል እንደተናገሩት በስፋት የተዳሰሱት እንግዶች ወደ ሆቴል በሚመጡበት ወቅት ከኮቪድ-19 ስጋት ነጻ ሆነው ቆይታቸው አስደሳች እንዲያ-ደርጉ የሚሰጡ አገልግሎቶች ከፍተኛ ጥንቃቄ በተሞላበትና ንጽህናውን በጠበቀ መልኩ ለእንግዳው ወይም ለደንበኛው እንዲሰጡ የሚያደረግ የማነቃቃት ስራዎች እንደተሰሩ ገል-ጸዋል።



ስልጠናና ማማከር አገልግሎት ካገኙት ከተሞች ቢሾፍቱና አዳማ የሚገኙ ሲሆን በከተማው ካሉ ከ40 በላይ ሆቴሎች መካከል በተሻለ ደረጃ ኮቪድ19ን የመከላለል ስራ እየሰሩ ያሉ የቢሾፍቱ የቱ፣ ሮዝሜሪ፣ ሌክ ብሾፍቱ ሪዞርት ሆቴሎች ሲሆኑ በአዳማ ካራዩ ሪዞርት መሆ-ናቸውን ተመልክተናል። በተመሳሳይ የጥንቃቄ ጉድለት የታየባቸውም በአዳማ መስቀል ክትፎ ቤት፣ ኬሮድ ሬስቶራንት የመሳሰሉት የታዩ ቢሆንም ክፍተቶቻቸውን ለማስተካከል በሙሉ ፍቃደኝነት ስልጠናውንና ምክሩን ተቀብለዋል።

ከቀጣይ ገጽ ...



የቢሾፍቱ የቱ ሆቴል ስራ አስኪያጅ አቶ ፍቃዱ ጣሴ እንደተናገሩት ኮቪድ19 በመምጣቱ ተቋሙ በብዙ እንደተጎዳና ለማንሰራራት ብዙ ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ጠቁመው የተሰጠው ስልጠናና የምክር አገልግሎት እንደሚያነቃቸው ገልጸዋል፡፡
የሌክ ብሾፍቱ ሪዞርት ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ እየሩሳሌም ከበደ እንደተናገሩት ማሰልጠኛ ተቋሙ ቀድሞ እንደዚህ አይነት ስልጠናዎችንና ማማከር ስራዎችን ቢሰጠን ጥሩ እንደነበር በመግለጽ እኛ በራሳችን ጥረት እየሰራንም የተጓደሉብንን ለማሟላትና ሰራተኞቻችን ለማንቃት ስልጠናው ጠቀሜታ አለው ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ የተሰጠው ስልጠናና የማማከር አገልግሎት ጠቀሜታው ለእንግዶች፣ ለጎብኝዎች፣ ለሰራተኞች፣ ለአከባቢው ማህበረሰብ እና በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሙያዎች እንዲሁም በዘርፉ የተጎዱ ሆቴሎች እና ቱሪስት መዳረሻ-ዎች ሲሆን፤በኮቪድ19 ምክንያት የተቋረጠውን የሆቴልና ቱሪዝም የንግድ እንቅስቃሴ እንዲቀጥል የሚያስችል መሆኑም ተገልጸዋል፡፡





የኮሮና ቫይረስ ወርሽኝ በሀገራችን የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ላይ ያደረሰው ተፅዕኖና የቀጣይ መፍትሔ አቅጣጫን የሚ-ጠቁም ጥናት ይፋ ተደርጓል፡፡
ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ነሐሴ 21/2012

በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ባለቤትነት የተጠናው ጥናት የኮቪድ-19 ቫይረስ ወረርሽኝ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፎች ላይ ያደረሰውን ተጽእኖ በመለየት በቀጣይ ቢደረግ የሚገባውን የመፍትሔ አቅጣጫ በሚያመላክት መልኩ አቅርበዋል፡፡
በጉባኤው ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉትየባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ሂሩት ካሳው ጥናቱ በዘፈቀደ፣ በተናጥልና ባልተደራጀ መልኩ ይገለጽ የነበረውን የኮቪድ-19 ተጽዕኖ ጥናትን መሠረት በማድረግ በእርግጠኝነትና በተጨ-ባጭነት በአሃዛዊ ለመግለጽ ከማስቻሉም በላይ በቀጣይ ልናከናውነው የሚገባውን የመፍትሔ አቅጣጫ ያመላክታል ብለዋል፡፡
የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ በበኩላቸው ጥናቱን ለማካሄድ በሁሉም የቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች በመገኘት በተጨባጭ መረጃ በመመስረት የተጠና ጥናት መሆኑን ገልጸዋል፡፡
የማሰልጠኛ ማዕከሉ አካዳሚክና ምርምር ዲን
አቶ ግሩም ግርማ ተቋሙ በየአመቱ በርካታ የጥናት ስራዎች እየተሠሩ ሲሆን በቀጣይ አስር አመታት ከ80 የማያንሱ የዘርፉን ችግር የሚፈቱ ሀገራዊ የጥናትና ምርምር ስራዎች ለመስራት በዕቅድ መያዙን ገልጸዋል፡፡



የማሰልጠኛ ማዕከሉ በመከላከያ ስታፍ ኮሌጅ ለሚሰሩ የምግብ ዝግጅት ባለሙያዎች አጭር ስልጠና ሰጠ፡፡
ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ማ ጥቅምት 05 /2013 ዓ.ም

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል በመከላከያ ስታፍ ኮሌጅ ለሚሰሩ የምግብ ዝግጅት ባለሙያዎች በምግብ ዝግጅት፣ በምግብና መጠጥ መስተንግዶ እና በንጽህና አጠባበቅ (hygiene) 19 ለሚሆኑ ሙያተኞች የአጭር ጊዜ ስልጠና ሰጠ፡፡
የምስክር ወረቀት አሰጣጥ መርሐ ግብር ላይ የተገኙት የማዕከሉ የአካዳሚክ ዲን ተወካይና አጫጭርና ተከታ-ታይ ትምህርት ክፍል ኃላፊ አቶ ይታሰብ ስዩም የማ-ሰልጠኛ ተቋሙ በተለያዩ በስልጠና፣ በጥናትና ምርምር እና ማማከር አገልገሎት የሀምሳ አመት ልምድ ያለው መሆኑን ገልጸው ለወደፊት በስልጠናና ሙያዊ እገዛዎ-ችን ለማድረግ ዝግጁ ነን ብለዋል፡፡

በመከላከያ አዛዥነትና ስታፍ ኮሌጅ አዛዥ ጀኔራል ዳኛቸው ይትባረክ በበኩላቸው በማሰልጠኛ ማዕከሉ ለምግብ ዝግጅት ባለሙያዎች የተሰጠው ስልጠና ለተማሪዎቻችን የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ያስች-ለናል ብለዋል፡፡ የመከላከያ አዛዥነትና ስታፍ ኮሌጁ ለወደፊት ተመሳሳይ ስልጠናዎችን እንደሚያዘጋጅም ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም ጀኔራል ዳኛቸው ይትባረክ የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ለሰጠው ስልጠናና የማማከር አገልግሎት ምስጋና አቅርበዋል፡፡










5% OFF







# የሆቴልና ቱሪዝም
## ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል

**CATERING AND TOURISM TRAINING CENTER**

follow us

www.ctti.edu.et

Catering & Tourism Training Institute

ከኮሮና ቫይረስ ራሴን እጠብቃለሁ
እራሱን የሚጠብቅ ሌሎችን ያድናል!